የሻሸመኔ ከተማ

የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድና አያያዝ ተሞክሮ









ህዳር
2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
Ethiopian Environmental Protection Authority
epa.gov.et

ማውጫ

1. ክፍል አንድ 1

1.1 ዓላማ 1

1.1.1 ዋና ዓላማ 1

1.1.2 ዝርዝር ዓላማዎች 1

1.2 አስፈላጊነት 1

1.3 ወሰን 1

1.4 ተሞክሮውን ለመቀመር መረጃ ያሰባሰበው ቡድን 1

1.5 የመረጃ አሰባሰብ ስልት 2

1.6 የሚጠበቁ ውጤቶች፡- 3

2. ክፍል ሁለት 4

2.1 የሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር 4

2.1.1 የሻሸመኔ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ከመጀመሩ በፊትየነበረበት ሁኔታ *4*

2.1.2 የተከናወኑ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት 4

2.1.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 5

2.2 ቴክኖሎጂ አጠቃቀም 6

2.3 በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማስወገድ ስራ ላይ ለመስራት የተደራጁ ማሕበራት 7

2.4 የውሃ መውረጃ ቦይ ጽዳት 11

2.4.1 የዲደ ቡቂ ማህበር 11

2.5 የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (LAND FILL) 12

2.6 በከተማው ከተከናወኑ የቆሻሻ ማስወገድ ስራ ውስጥ በተሞክሮነት የሚወሰዱ ስራዎች 14

2.6.1 ሞዴል መንደሮች መመረጣቸው 14

2.7 የአረንጓዴ ልማት ስራ 15

2.7.1 የወንዝ ዳርቻ ልማት 15

3. ክፍል ሦስት 17

ማጠቃለያ 17

መግቢያ

ኢትዮጵያ በ2030 የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለመሆን በምታደርገው ጥረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዜጎች በህገ መንግስቱ አንቀፅ 44 የተደነገገውን በንጹህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት ለማረጋገጥ እንዲሁም ከሁሉም የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር ተያይዞ በአካባቢ ላይ ሊከሰት የሚችል አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲቀንስና በዘርፉ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያግዙ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማዘጋጀት በርካታ የአካባቢ ጥበቃ ተግበራትን እያከናወነ ይገኛል።

የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድና አያያዝ ጉድለት የአብዛኞቹ የሀገራችን ከተሞች ችግር እንደሆነ ይታወቃል። ለዚህም ምክንያት ከሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የግንዛቤ ክፍተት መኖር ፣ የህዝብ ቁጥር መጨመር ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የህዝብ ፍልሰት ፣ የከተማ ፕላንን መሰረት ያላደረገ ህገወጥ የቤቶች ግንባታ ፣ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ጋር በተየያዘ መሰረተልማቶች አለመስፋፋት እንዲሁም ከህግ አተገባበርና ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ክፍተት መኖር እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ።

በመሆኑም ጉድለቶቹን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ባለመዘርጋቱ ከተሞችን ጽዱና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት እያደናቀፈ ይገኛል። በየከተሞች የሚታየዉ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ዝቅተኛ መሆን ነዋሪዎችን ለተለያዩ ተላላፊ እና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ተጋላጭ እያደረገ ስለሚገኝ ዋነኛ የቅሬታ ምንጭ ሊሆን ችሏል።

የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በከተሞች የሚከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አሰራር ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ ቀጣይ ለሚደረጉ የግንዛቤ ማስፋፊያ ሥራዎች በግብዓትነት ለመጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል።

በመሆኑም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ካሉት የከተማ አስተዳደሮች አንዱ በሆነችው የሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድና አያያዝ ስርዓትን በማሻሻል ቆሻሻውን ከቤት ለቤት ልየታ ጀምሮ እስከ ቆሻሻ ማስወገጃ ያለውን ሂደት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የተከናወኑ ተግባራቶች ለሌሎች አስተማሪ በመሆናቸው ለመልካም ተሞክሮ የሚሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ይህ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

ክፍል አንድ

1.1 ዓላማ

1.1.1 ዋና ዓላማ

በከተማ ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ያለውን መልካም ተሞክሮ በማሰባሰብ፣ በመለየትና በመቀመር ወደ ሌሎቹ እንዲስፋፉ ማድረግ፣

1.1.2 ዝርዝር ዓላማዎች

1.1.2.1 የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓትን በማዘመን አካባቢን ጽዱና አረንጓዴ ለማድረግ ዜጎች የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ ፣

1.1.2.2 ቆሻሻ ሀብት መሆኑን በመረዳት ዜጎች በዚህ ሀብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማበረታታትና ለማስፋፋት፣

1.2 አስፈላጊነት

ከተሞችን ጽዱና አረንጓዴ የማድረግ መልካም ተሞክሮዎችን ቀምሮ ሌሎች እንዲማሩበትና እንዲጠቀሙበት በማድረግ ፣ ምቹ አካባቢን መፍጠር ፣ እንዲሁም የህብረተሰብን ጤና ማሻሻልና ፣ ቱሪዝምን በማሳደግና በአጠቃላይ አካባቢን ከመጠበቅ አኳያ ጠቀሜታዉ የጎላ ነዉ ።

1.3 ወሰን

የተሞክሮ ቅመራው የተከናወነው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የተከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ተግባራትን በአሰራርና ውጤታቸው አርዓያ በሆኑት ስራዎች ላይ ያተኮረ ነው።

1.4 ተሞክሮውን ለመቀመር መረጃ ያሰባሰበው ቡድን

መረጃ የመሰብሰብ ፣ የማደራጀትና ተሞክሮ የመቀመር ስራዎች በፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ መብቶች ግንዛቤ ማጎልበቻ ዴስክ የተውጣጡ ሦስት ባለሙያዎች ሲሆኑ በተጨማሪም ዝርዝር ሁኔታን በማስረዳት ከሻሸመኔ ከከተማ አስተዳደሩ የተዉጣጡ ሦስት ባለሙያዎችም ተሳትፈዋል።



ፎቶ 1፡- መረጃ ያሰባሰበው ቡድን

1.5 የመረጃ አሰባሰብ ስልት

የአካባቢ መብቶች ግንዛቤ ማጎልበቻ ዲስክ ባለሙያዎች ተሞክሮውን ለማሰባሰብ የሚረዳ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት አስቀድሞ ለክልልና ለከተማ አስተዳደሩ በኢሜል በመላክ ይዘቱን ቀድመው እንዲያውቁት በማድረግ ነው።

በመቀጠልም የባለሙያዎች ቡድን በሥራው ላይ እንደተሠማራ በቅድሚያ ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና ከከተማ አስተዳደሩ አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ስለ ተልዕኮው ዝርዝር ሁኔታ በመወያየት የተሻለ ተሞክሮ ይገኝባቸዋል ተብለዉ በተመረጠው ቦታዎች በመንቀሳቀስ መረጃ ተሰባስቧል።

የመረጃ አሰባሰቡ ሂደቱም የተዘጋጀውን ቼክ ሊስት በመጠቀም ሲሆን ለዚሁ ተግባር የሚጠቅሙ ሰነዶችን በማገላበጥ፣የማህበር አባላትንና ሌሎች ተጠቃሚዎችንና ባለሙያዎችን በማነጋገር እና ሥራው በሚከናወንበት ቦታ ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ነው።

በመጨረሻም ከሻሸመኔ ከተማ አስተዳደሩ ማዘጋጃና አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመስክ ምልከታው በታዩና በተነሱ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት በማካሄድ ተጨማሪ መረጃም ተወስዷል።



ፎቶ 2 ፡- መረጃ ሲሰበሰብ

1.6 የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የተቀመረውን መልካም ተሞክሮ በግብዓትነት በመጠቀም ግንዛቤ ያሳድጋል።
- ይህ መልካም ተሞክሮ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎች በአስተማሪነት ለሌሎች ቀርቦ ይጠቀሙበታል።
- ሌሎች ቦታዎች ይህንን ተሞክሮ በግብአት በመጠቀም ከአካባቢያቸዉ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር አካባቢያቸውን ጽዱ ያደርጋሉ።
- የተለያዩ ቴክኖለጂዎችን እና ሳይንሳዊ መንገዶችን በመጠቀም ቆሻሻን ወደ ሃብት መቀየር እንደሚቻል ሕብረተሰቡ በተግባር ይረዳል።
- ከስራ እድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ ገቢን ያሳድጋል።
- አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎች በስፋት እንዲተገበሩ ይረዳል።
- በአጠቃላይ የሰርኩላር ኤኮኖሚን ስልት ለመተግበር ይረዳል።

2 ክፍል ሁለት

2.1 የሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር

የሻሸመኔ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ አርሲ ዞን ከአዲስ አበባ 250 ኪ.ሜ.ርቀት ላይ ትገኛለች።ከተማዋ 17,119 ሄክታር ስፋት አላት።

ሻሸመኔ ከተማ በ1903 ዓ.ም. የተመሠረተች ስትሆን የምዕራብ አርሲ ዞን ዋና ከተማ ስትሆን ሻሸመኔ የሚለውን ስያሜ ያገኘችው ‹‹ሻሼ›› የምትባል በአካባቢው ለሚተላለፉ መንገደኞች ምግብ፣መጠጥ፣ የመሳሰሉ ነገሮችን ከምታቀርብ ሴት ነጋዴ ስም የተወሰደ ነዉ። ስለዚህ የሻሼ ቤት (መኒ-ሻሼ) ከሚለው ተወስዶ እስከዛሬ ድረስ ‹‹ሻሸመኔ›› በመባል ከተማዋ ትጠራለች (Katabo,1999)።

ከተማዋ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓትን በመፍጠር በፊት ከነበረችበት ኋላቀር የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ተላቃ አሁን የተሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ካላቸው ከተሞች መካከል አንዱ ልትሆን ችላለች።

2.1.1 የሻሸመኔ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ከመጀመሩ በፊትየነበረበት ሁኔታ

በሻሸመኔ ከተማ የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ከመጀመሩ በፊት የቆሻሻ አያያዝ ሥርዓቱ ከተማዋን በሚመጥን ፣ የህብረተሰቡን ጤና እና ስነምህዳሩን ታሳቢ ያላደረገ በመሆኑ በአካባቢው አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድር ነበር። በከተማው ውስጥ ቆሻሻ በዘፈቀደ ከመጣሉም በላይ የቆሻሻ ገንዳዎች በቂ ጥና ት ሳይደረግባቸዉ በመቀመጣቸዉ ከጥቅማቸዉ ይልቅ ጉዳታቸዉ ያመዝን ነበር።ይህም ሊሆን የቻለዉ ቆሻሻ ሳይለይ በአንድ ላይ ስለሚከማች ገንዳዎች ሞልተዉ ቆሻሻዉ እስኪወገድ ድረስ ባሉ ጊዚያት ዉስጥ መጥፎ ሽታ በመፍጠር የቆሻሻ ገንዳዎች በተቀመጡበት አካባቢዎች በሚኖሩ እና በሚያልፉ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ የጤና ፣የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ይደርስባቸው ነበር። በህብረተሰቡ ዉስጥ ቆሻሻ ጉዳት ብቻ እንጂ ምንም ጥቅም እንደሌለው አድረጎ የማሰብ፣ የፅዳት ተግባራትም የሌሎች አካላት ብቻ እንደሆነ የማሰብ ዝንባሌ እንደነበረ መረዳት ተችሏል።

2.1.2 የተከናወኑ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት

ከተማው የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ለማከናወን በመጀመሪያ ለአመራሮች ግንዛቤ የማሳደግ ስራ የተሰራ ሲሆን በመቀጠልም ለከተማው ለተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ለሐይማኖት ተቋማት እና ለመንግስት ሰራተኞች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል። አካባቢ ማጽዳት የሁሉም ኃላፊነት ስለመሆኑ ፣ ቆሻሻን በአግባቡ የመያዝ ባህልን በማሳደግ እንዴት ወደ ሃብትነት መቀየር እንደሚቻል በእነዚህ እና በመሳሰሉ ጉዳች ላይ ትኩረት በማድረግ ስልጠና ተሰጥቷል። ከዚህ ጋር በማያያዝም የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ተግባርን በአግባቡ ለመምራት የከተማው መዘጋጃ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በመተባበር በዚህ ስራ ላይ የሚሰማሩ ማህበራትን በማደራጀት ወደ ተግባር እንዲገቡ አድርገዋል ። ማህበራቱ ስራ ከመጀመራቸው በፊት ከከተማ አስተዳደሩ ማዘጋጃ ቤት የውል ስምምነት ተፈራርመዋል። የስምምነታቸዉ አጠቃላይ ይዘት የከተማ አስተዳደሩ ማዘጋጃ ቤት በሚያስፈልጉ ነገሮች ላይ ማህበራቶችን ሊደግፍና የስራ ቦታ ሊያመቻች እንዲሁም ማህበራቶች ደግሞ የተሰማሩበትን ስራ እንደየስራ ድርሻቸው በአግባቡ ማከናወን የሚሉ ጉዳዮች ሲሆኑ በነዚህ ዉልና ግዴታዎች ላይ በመግባባት ወደስራ ሊገቡ ችለዋል።
ሥራውን ለማከናወን የሚረዱ የታቀዱ ዝርዝር ተግባራት የሚከተሉት ናቸዉ።

- ለአመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠር ፣

- ሕብረተሰቡ ከመኖሪያቸው እስከ 20 ሜትር ርቀት አካባቢያቸውን እንዲያፀዱ ማድረግ ፣
- ተቋማትና ድርጅቶች እስከ 50 ሜትር ርቀት አካባቢያቸውን እንዲያፀዱ ማድረግ ፣
- ቆሻሻ በየአይነቱ እንዲለይ ማድረግ ፣
- የቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና መልሶ መጠቀም ስራን ማጠናከር ፣
- የማሕበረሰብ አቀፍ የንቅናቄ የፅዳት ዘመቻ ማካሄድ የሚሉ ይገኙበታል።

2.1.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ስራው ከመጀመሩ በፊት እና በሂደት ላይ እያለ የታቀዱ የግንዛቤ ስራዎችን መነሻ በማድረግ ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ የተሰራ ሲሆን ትኩረቱም

- የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ፣
- ቆሻሻ እንዴት ከምንጩ መቀነስ እንደሚቻል፣
- ቆሻሻን በአይነት የመለየት፣
- ቆሻሻን የመሰብሰብ ስራ በአግባቡ ከተሰራ ወደሃብት መቀየር እንደሚቻል፡ ፣
- አካባቢን ማጽዳትና መንከባከብ የሁሉም ድርሻ መሆን እንዳለበት በሚሉ ርዕሶቹ ዙሪያ በርካታ ማህበረሰብ ተሳታፊ ማድረግ ተችሏል።

ስራውን በተቀላጠፈ መንገድ ለማከናወን ለማህበራት ድጋፍና ክትትል በማድረግ ማህበራትን ማጠናከር የተቻለ ሲሆን በውሉ እና በስምምነቱ መሰረት ስራው በመከናወን ላይ ይገኛል። በተጨማሪም በቆሻሻ ተበክሎ የነበረን የወንዝ ዳርቻ በማልማት ወደ መዝናኛ ስፍራ በመቀየር አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል።

አባሪ 1. ለግንዛቤ ተዘጋጅቶ የተሰራጨና ስራ ላይ የዋለ ጽሁፍ

1/03/2015

ማስታወቂያ

ከተማችን ስእኛዉ በእኛዉ ትፀዳለች!!

1. በሀገሪቷ ሕገ መንግስት አንቀፅ 44 ቁጥር 1 መሠረት ሁሉም ሰዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸዉ፡፡ በዚሁ ሕገ መንግስት አንቀፅ 92 ቁጥር 4 መሠረት መንግስትና ዜጎች አካባቢያቸዉን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸዉ፡፡
2. ማንኛዉም ሰዉ የመኖሪያ ቤቱን ፊስፍትና ዙሪያ 20 ሜትር የማፅዳት ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛዉም ድርጅት ያለዉ ሰዉ የድርጅቱን ፊስፍትና ዙሪያ 50 ሜትር የማፅዳት ግዴታ አለበት፡፡
4. ማንኛዉም ሰዉ/ድርጅት ከቤቱ/ከድርጅቱ የሚወጣዉን ቆሻሻ በአግባቡ የመያዝና የማስወገድ ግዴታ አለበት፡፡የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጅ ቁጥር 513/1999 በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ላይ ችግር የፈጠረ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 300/1995 አካባቢውን በደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ የበከለ የገንዘብ ቅጣት ከ 80.00ብር እስከ 20,000.00 ብር እና የእስር ቅጣት ከ 15 ቀን እስከ 5 ዓመት እንደ ጥፋቱ ክብደት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፤
5. ማንኛዉም ሰዉ የቀንድ ከብት፤ ፈረስና አህያ እንዲሁም በግና ፍየል በየትኛዉም የከተማ ክልል ዉስጥ መልቀቅ የለበትም፡፡ ተለቀዉ ቢገኙ 81 የበግ ተራ ጎን በሚገኝ ቦታ ላይ በማቆየት፡-
   - የቀንድ ከብት፤ ፈረስና አህያ 200.00 (ሁለት መቶ) ብር ይቀጣሉ፤ ባደረ ቁጥር በእጥፍ ይጨምራል፡፡
   - በግና ፍየል 100.00 (አንድ መቶ) ብር ይቀጣሉ፤ ባደረ ቁጥር በእጥፍ ይጨምራል፡፡
6. ማንኛዉም ሰዉ በአህያ ጋሪ፤ በኩሩኩሩ ጋሪ እና በማንኛዉም ነገር ቆሻሻን ከተማ ዉስጥ መጣል የለበትም፤ ጥሎ ቢገኝ 500.00 (አምስት መቶ) ብር ይቀጣል፡፡
7. ማንኛዉም ሰዉ በግንባታ ምክንያት በህዝብ መንገድ ላይ የግንባታ ዕቃዎችን ማስትም ድንጋይ፤ አሸዋ፤ አፈር፤ እንጨትና የተሰያዩ ዕቃዎችን ማስቀመጥ አይችልም፤ ያስቀመጡም ካሉ በሰጮር ጊዜ ዉስጥ እንዲያነሱ እያስጠነቀቅን በማያነሱት ላይ በህጉ መሠረት እርምጃ የሚንወስድ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

ስለዚህ የተከበራችሁ የከተማችን ነዋሪዎች ከተማችንን ፅዱ፤ ዉብና አረንጓዴ ለማድረግ ሁሳችንም የበኩሳችንን ድርሻ እንዲናበረክት ጥሪያችንን በአክብሮት እያስተሳስፍን ይህ ማስታወቂያ ከተሰጠፈና ከተነገረ ዕስት ጀምሮ አሳይ የተቀመጡትን መመሪያዎች ጥሶ በተገኘ ሳይ እርምጃ ስመዉሰድ የምንገደድ መሆኑን እንገልጻስን፡፡

የሻሸመኔ ከተማ ማዘጋጃ ቤት

2.2 ቴክኖሎጂ አጠቃቀም

የሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር ከጊዜ ወደ ጊዜ በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ላይ ያለውን ትኩረት በመጨመር ስራውን በሚያከናዉንበት ጊዜ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ጎን ለጎን መጠቀም ችለዋል።ከተማ አስተዳደሩ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎችን በተለያዩ ቦታዎች በማስቀመጥ፣ ከሚበሰብሱ ቆሻሻዎች ኮምፖስት ማዘጋጀትና፣ መልሰዉ ጥቅም ላይ የሚዉሉትን ለፋብሪካዎች በማስረከብ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ማድረግ ተችሏል።

በከተማው ማዘጋጃ ቤት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ጉድፍ ማጠራቀሚያ (ደስት ቢን) ከአቅራቢ ማህበራት በመግዛት በየመንደሩ በማከፋፈል ለአገልግሎት ምቹ በሆኑ ቦታዎች እንዲቀመጡ የተደረገ ሲሆን የከተማዉ ማህበረሰብ በአቅራቢያቸዉ ባሉ የጉድፍ ማጠራቀሚያዎች ዉስጥ ደረቅ ቆሻሻን እንዲጥሉ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በሻሸመኔ ከተማ 90 ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች (ደስት ቢኖች) አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህ ጉድፍ ማጠራቀሚያዎች (ደስት ቢንኖች) ዉስጥ

የተጠራቀመዉን ቆሻሻ በየቀኑ ወደ ማስወገጃ ቦታ ይወሰዳል። እነዚህ ጉድፍ መጣያዎች ተደራሽ ባልሆኑባቸዉ አካባቢዎች ዉስጥ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻው በግቢያቸዉ ዉስጥ በማጠራቀሚያ ከረጢት ዉስጥ እንዲያጠራቅሙ በማድረግ ለሚሰበስቡ ማሕበራት በየቀኑ ያስረክባል።

በተጨማሪም ቆሻሻ የሚሰበስቡ ማህበራት መልሰዉ ጥቅም ላይ ሊዉሉ የሚችሉ የፕላስቲክ ዉጤት የሆኑ ቆሻሻዎችን ለይተዉ በመሰብሰብ እና ከሚሰበስቡ ግለሰቦች 1ኪ.ግ በ10 ብር በመረከብ ለሌላ ድርጅቶች 1ኪ.ግ በ22 ብር በማስረከብ ላይ ይገኛሉ። እንዲሁም ወደ ቀልዝነት መቀየር የሚችሉ ቆሻሻዎችን በመለየት ሰፋ ባለ ሁኔታ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት እየተሰራ ይገኛል።



ፎቶ 3 የቴክኖሎጂ ስራዎች

2.3 በደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማስወገድ ስራ ላይ ለመስራት የተደራጁ ማሕበራት

ተ.ቁ	የማህበር ስም	ብዛት	ወ	ሴ	ድ
1	የመንገድ ላይ ጽዳት ስራ	16	17	270	287
2	የከተማ አረንጓዴ ልማት	2	13	25	38
3	የቦይ ውስጥ ጽዳት ስራ	3	87	6	93
4	ህግ አስከባሪዎች	1	20		20
5	የትራክተር ረዳት ቆሻሻ ጫኚ	5	45	4	49

6	ቤት ለቤት ቆሻሻ ሰብሳቢ	11	78	61	139
7	ቆሻሻ መልሶ መጠቀም	2	5	25	30
	ድምር	40	265	391	656


ሠንጠረዥ1 በተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የተደራጁ ማህበራት



ፎቶ 4 በጽዳት ስራ የተደራጁ ማህበራት

የማህበር አባላት ክፍያን በተመለከተ በወርሀዊ ደመወዝ ሆኖ ዝቅተኛው 1200 **እና ከፍተኛው** 10000 **ብር ሲሆን ከተለያዩ ቁርጥራጭ ብረቶችና ከመሳሰሉት ሽያጭ ተጨማሪ ገቢ የሚያገኙበት ሁኔታ አለ።ከህብረተሰቡ ድርሻ ጋር በተያያዘ የአገልግሎት ክፍያ መፈፀም ሲሆን ከያንዳንዱ ቤተሰብ እና ከያንዳንዱ ተቋም በየወሩ ከ**80 **እስከ** 200 **ብር በማህበሩ ተሰብስቦ ገቢ ይሆናል። ማህበራቱ ተግባራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጓቸዉን መሳሪያዎች የከተማ አስተዳደሩ ከ** USAID **በተባለው አለም አቀፍ ድርጅት ባገኘዉ የገንዘብ ድጋፍ** 40 **ጋሪዎች ፣** 3 **ሲኖትራክ ፣** 2 **ገንዳ የሚያጓጉዝ ስኪፕ ሎደር ፣** 1**ግሬደር ፣** 5 **ቆሻሻ የሚያነሱ ትራክተሮችን በመግዛት ድጋፍ አድርጎላቸዋል።**

አባሪ 2.ውል መፈጸሚያ ቅጽ



Waldaa Sharikummaa Maayikiroo
ጀማል፤እየሩስአሌም፤ተስፋዬአና ገደኞቻቻዉ Jamaal, [illegible]alem,Tasfayyee fi Hiriyoota Isaanii
የደረቅ ቆሻሻመሰብሰብ እና መልሶ መጠቀም Hojii Tajaajila Qulqullina Balfaa Gogaa
ሻሸመኔ Funaanuu Fi Deebisanii Fayyadamuu
Shaa/nnee

ቀን----------

ከ ከተማ ማህብረሠብ አና ቤት ለቤት ቆሻሻን ከሚሰበስቡ ማህበራት ጋር የሚደረግ የስምምነት ቅጽ

- ከተማ፡ ሻሻመኔ
- ቀበK? : **አሌሉ**
- የድርጅት /የአባወራ/ ሥም _____ ሀ/ ንግድ ለ/ መኖሪያ ቤት
  ሐ/ የተለያየ ድሪጅት
- ለቤቱ የተሰጠ መለያ ቁጥር _____
- የሚሰጠው አገልግሎት **<u>የደረቅ ቆሻሽ ከመኖሪያ ቤት መሰብሰብ</u>**
- የቤት ቁጥር _____
- የሥልክ ቁጥር _____
- የሚየመሪተዉ /የሚመነጨው የቆሻሻ መጠን _____
  - ✓ ለመኖሪየ/ድሪጅት/ ቤት በኩነታል _____ ብር
    _____(_____)
  - ✓ በመኖሪያ ቤቱ የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ በሳምንት አንድ ግዜ እና ከ$አ^3$ በላይ ማንሳት
  - ✓ በ ሳምንት _____ብር (_____)
  - ✓ በ ወር _____ብር (_____)
  - ✓ የክፍያ ግዜ የሚጀመርበት ቀን ----------ሆኖ በየ 15 ቀን የሚከፈል የሆናል

1. **<u>የቆሻሻ አመንጭዎች ግዴታዎች</u>**
   - ✓ የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ በፈርጁ ለይቶ ማዘጋጀት
   - ✓ የሚጠበቅባቸዉን ክፍያ በዉሉ መሰረት መፈጸም

   በማኅበራቶች በኩል የተሰጡትን የቆሻሻ መስቀመጫ/ማጠራቀሚያ/ ዕቃ በአግባቡ መያዝ እና ለተበለለት አገልግሎተ ብቻ ማዋል ።
   ከመኖር ቤታቸዉ ዉስጥ የሚመነጨዉ ደረቅ ቆሻሻ እና ቤታቸዉ እስከ 20 ሜትር ራዲየስ ዉስጥ የለዉን ቦታ መጽዳትና የመጣበቅ አለበቸዉ ።
2. **<u>የማህበራት ግዴታ።</u>**
   - ➢ ቆሻሻ ተላይተዉ የT>ቀSጥበትን እቃ ማዘጋጀት
   - ➢ ተለይተዉ የተቀመጠዉን ቆሻሻ በግዜ ማንሳት
   - ➢ ቆሻሻ የሚነሰባት ቀን _____
   - ➢ ክፍያዉን በዉል ስምምነት መሰረት ግዜዉን ጠብቀዉ መዉሰድ ።
   - ➢ ዉል ሰጪና ተቀባይ ስምምነቱን ለመፍረስ ከፈለጉ ቀደም ብሎ ከአንድ ወር በፊት ማሰወቅ አለበቸዉ።

3. ይህን ዉል የፊረሰ በፍ/ህግ/ስነ-ሰርዓት 1679 እና 1980 ንዑስ አንቀፅ (አንድ) መሰረት ዉሉን ለከበረ 500.00 ብር (አምስት መቶ ብር)ይቀጣል።አ"Ç=ሁም ለመንግስት 500.00 ብር (አመስት መቶ ብር)ተቀጥተው ዉሉ የጸና ይሆናል።

የቆሻሻ አመንሴዎች **የማህበሩ**

ያረጋገጠ

ስም ---------- ስም ---------- ስም ----------

ፍርማ ---------- ፍርማ ---------- ፍርማ ----------

ቀን ---------- ቀን ---------- ቀን ----------

አባሪ 3.

Guyyaa _____

Formii Woligaltee Hawaasa Magaala fi Waldaa Balfaa Mana Manaa Kaasan Wajjiin Taasifamu .

- ✓ Magaalaa Shaashamannee:
- ✓ Gandaa _____
- ✓ Maqaa Dhaabbataa/ abba worraa _____
- ✓ A. Daldala B. Mana Jireenya C. Dhaabbile Garagaraa.
- ✓ Kodii manichaaf kenname _____
- ✓ Tajaajila kennamuu Balfaa Guyyaa Guyyaan Sadarkaa Maatiti Omishamu Addaan Baasan Kaasu.
- ✓ Lakk Mana/Daldalaa/_____
- ✓ Lakk Bilbilaa _____
- ✓ Hamma Balfa Inni Oomishuu :-
  - M/Jireenyaatiif Kuntaalaan _____Qar,_____(_____)
  - Balfaa sadarkaa matii mana sanaati omishamee torbeetti al tokko fi isaa ol kaasuu
  - Torbanitti Qarshii _____(_____)
  - Ji'atti Qarshii _____(_____)
  - Yeroo kafaltii _____ irraa kan eegalu ta'e kafaltiin guyyaa *15(Kudha shan)* al tokko ni kafalama .

❖ Dirqama Balfa Maddisiiftota:-

- ✓ Balfa madisisan adda baasani qopheesuu
- ✓ Kafalti isaani irra eegamuu akkaataa waligalameen kanfaluu
- ✓ Meshaalee gama waldichaatiin kennemeef seraan qabachuu fi tajaajila jedhameef qofa olchuu qabu.

- ✓ Balfa Goggogaa Mana jireenyaa keessaa fi afoo Mana jireenyaa isaani hanga *raadiyeesii 20m* qulqulleessuu qabu

❖ **Dirqama Woldichaa**:

- ✓ Meshaalee balfaan itti adda bahee ka'amu ni qophessaa
- ✓ Balfa adda bahee qophaa'ee yeroon kaasuu
- ✓ Guyyaa Balfichaa itti ka'uu _____
- ✓ Kafalti akkaata waligalameen yeroo isaa eeganii fudhachuu

Ahaadii kenna fi **Ahaadii fudhataan** waligaltee kan diiguu yoo barbaadan ***ji'aa 1(tokko)***dura dursanii beeksisuu qabu. Qaamni waliigaltee kana diigee BSHH **1679** fI **1680(1)**qaama waliigaltee kabajeef ***qarshii 500 (dhibba shan***) ni adabama akkaasummaas Mootummaafis ***qarshii 500(dhibba shan)*** ni adabama.

❖ Mallattoo Balfa Maddisiiftota Mallattoo Woldichaa Raggaasisee M/Q

_____ _____ _____

2.4 የውሃ መውረጃ ቦይ ጽዳት

የዉሃ መዉረጃ ቦይ ፅዳት የሚከናወነዉ በተደራጁ ማህበራት ሲሆን እነዚህ ማህበራት ዲደ ቡቄ፣ አዋሾ እና አራዳ ናቸው።ከነዚህ ማህበራት ውስጥ ዲደ ቡቄን እንደ ማሳያነት መጥቀስ ይቻላል።

2.4.1 የዲደ ቡቄ ማህበር

ይህ ማህበር የተደራጀውና ስራ የጀመረው በ2006 **ዓ.ም ነው።ማህበሩ** 21 **አባላት ያሉት ሲሆን በቦይ ጽዳት ላይ ተሰማርተዉ ይገኛሉ።አባላቱ እየሰሩ ያሉት በቀን** 80 **ብር እየታሰበላቸው በወር** 2400 **ብር ይከፈላቸዋል።**



ፎቶ 5 የቦይ ጽዳት

2.5 የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (land fill)

በከተማው ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ የሽግግር ማእከል ባለመኖሩ ቆሻሻን ከጉድፍ መጠያ ውስጥ እንዲሁም ከተለያዩ ቦታዎች በመሰብሰብ በቀጥታ ወደ ቆሻሻ ማስወገጃው ቦታ ይወሰዳል።

ይኸው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች በሀሌሉ ወረዳ እና በጨቢ ዲደ ኛታ መንደር ይገኛል። በሀሌሉ ወረዳ የሚገኘው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ስፋቱ 0.5 ሄክታር ሲሆን ከከተማው በ5 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የተገነባ ነበር። ቆሻሻን በአይነት የመለየት ስራ የሚከናወነዉ በዚሁ ዉስጥ ሲሆን ከተለዩት ቆሻሻዎች መካከል የሚበሰብሱትን ወደ ኮምፖስትነት በመቀየር ለገበሬዎችና ለከተማ አስተዳደሩ በሽያጭ መልኩ ሲያቀርቡ እንዲሁም መልሰዉ ጥቅም ላይ የሚዉሉትን ደግሞ ለተረካቢ ድርጅቶች በማስረከብ ገቢ ማግኘት ችለዋል። በተጨማሪም ቀሪዉን ቆሻሻ በዚሁ ቦታ ተለይቶ እንዲወገድ ያደርጋሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከተማው ወደጎን እየሰፋ በመምጣቱና ከከተማዉ ያለዉ ርቀት እየቀረበ በመምጣቱ በቀጣይ በማህበረሰቡ ጤና ላይ ተፅኖ እያሳደረ በመሆኑ የከተማዉ ማህበረሰብ ቅሬታ ማቅረብ በመጀመሩ ሌላ አማራጭ ቦታ እንዲዘጋጅ አስፈልጓል ።



ፎቶ 6 በስራ ላይ ያለ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (LAND FILL)

በመሆኑም አዲስ ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ባለቦታ አዲስ ቦታ እየተዘጋጀ ይገኛል። ቦታውም በጨቢ ዲደ ኛታ የሚገኘው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ሲሆን አጠቃላይ ስፋቱ 10 ሄክታር የሚሸፍን ሲሆን በዉስጡም የኮምፖስት ማዘጋጃ ሼዶችን ያካተተ ነዉ። የሚገኘዉም ከከተማው በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ 12 ኪ.ሜ ርቀት ይገኛል። ስራው በ2013 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ግንባታዉ ባለመጠናቀቁ አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነ መገንዘብ ችለናል።ነገር ግን በአሁኑ አመት ግንባታዉ በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን አፈፃፀሙም 98% ደርሷል። በአጠቃላይ ይህ ግንባታ ስርገትን ከመከላከል አኳያ የታችኛዉ ወለል ሙሉ በሙሉ በጂኦሜንብሬን የተሸፈነና ዙሪያዉን በብሎኬት አጥር የታጠረ የመተላለፊያ መንገድ የተሰራለት እንዲሁም ዙሪያዉን በዛፎች ለመሸፈን የተለያዩ እፅዋቶች እንዲተከሉ ተደርጓል ተተክለዋል።



ፎቶ 7 እየተሰራ ያለ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (LAND FILL)

2.6 በከተማው ከተከናወኑ የቆሻሻ ማስወገድ ስራ ውስጥ በተሞክሮነት የሚወሰዱ ስራዎች

2.6.1 ሞዴል መንደሮች መመረጣቸው

በከተማው ስምንት የተመረጡ ሞዴል መንደሮች አሉ።እነሱም አራዳ፣ አቦስቶ፣ ኩየራ፣ ዲደ ቦቄ፣ አሌሉ፣ በ/ጉዲና፣ ቡለቻና አዋሾ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ የተሻሉ ተብለው 2 ሞዴል መንደሮች በዋናነት የተመረጡ ሲሆን የሚገኙትም በመልካ በዴሳ ወረዳ እና በአሌሉ ወረዳ ነው። ከነዚህ ሞዴል መንደሮች ውስጥ በቡድኑ የታየው በመልካ በዴሳ ወረዳ ያለው አቦስቶ መንደር ነው።

2.6.1.1 አቦስቶ መንደር

አቦስቶ መንደር የሚገኘው በመልካ በዴሳ ወረዳ ውስጥ ሲሆን 1205 አባወራ ይኖርበታል።ይህንን መንደር የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ለሦስተኛ ወገን ለጀይላን አማንና ጓደኞቹማሕበር በማስተላለፍ የተሻለ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን መዘርጋት ተችሏል ። ጀይላን፣አማንና ጓደኞቹ ማሕበር የተመሰረተዉ በ2013 ዓ.ም ሲሆን ይህ ማህበር ወንድ 28 ሴት 4 ድምር 32 አባላትን አቅፎ ይዞ ወደስራ መግባት የቻሉት በ2014 ዓ.ም ነው። የማህበሩ አስተባባሪ ጀይላን ሲሆን በኢንቫይሮንሜንታል ኢንጂነሪንግ በማስተርስ የተመረቀ በመሆኑ ስራውን በዕውቀት ለመምራት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ከዚሁ መንደር ዉስጥ ማህበሩ በየቀኑ 5 መኪና ቆሻሻ ይሰበስባል።ለዚህ አገልግሎት ሕብረተሰቡ በየወሩ በመኖሪያቤት ደረጃ 100 ብር እንዲሁም ደግሞ ተቋማት እስከ 6000 ድርስ እየከፈሉ እንደሚገኙ ማወቅ ተችሏል። ለማህበሩ አባላት ከ 2500 እስከ 4000 ብር በየወሩ የሚከፈላቸዉ ሲሆን በተጨማሪም ከተለያዩ ቁርጥራጭ ብረቶችና መልሰዉ ጥቅም ላይ ከሚዉሉ ነገሮች ሽይጭ ተጨማሪ ገቢ ያገኛሉ።

በዚህ ሞዴል መንደር ዉስጥ 38 የጉድፍ መጣያ የሚገኙ ሲሆን ይህ በመሆኑ በርካታ ጥቅሞች አስገኝቷል ለምሳሌ ያክል ቆሻሻ እንዳይቆይ ፣ የሕብረተሰቡ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ከረጢት ወጭን ቀንሷል ፣ የግቢ በር ማንኳኳት ከማስቀረቱ በተጨማሪም አላፊ አግዳሚ ሁሉ ቆሻሻ በአግባቡ እንዳይጥሉ ይረዳል። በዚህ ሞዴል መንደር ዉስጥ በመንገድ ላይ ቆሻሻ የሚጥል ሰው ከተገኘ ህብረተሰቡ ጥቆማ በመስጠት በማዘጋጃ ቤት በኩል ቅጣቱ ተፈፃሚ ይደረጋል። ቅጣት የሚጣልበት ሲሆን ቅጣቱም እንደ ቆሻሻው መጠን ይወሰናል ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ከ1000 እስከ 1500 ብር ቅጣት እንደሚጣልበት እንዲሁም በተደጋጋሚ ከሆነ እስከ 5000 ብር ቅጣቱ ሊደርስ ይችላል ። ነገር ግን የቆሻሻው መጠን በጣም አነስተኛ ከሆነ ከ50 እስከ 100 ብር ቅጣት ይጣልበታል።

ጀይላን፣ አማንና ጓደኞቹ ማህበር የጉድፍ መጠያ (ደስት ቢን) በማዘጋጀት ለከተማ ማዘጋጃ ቤት በመሸጥ በተለያዩ መንደሮች እንዲስፋፋ እያደረጉ ይገኛሉ ። ማህበሩ እስከአሁን ካዘጋጀው የጉድፍ መጠያ ውስጥ ለሻሸመኔ ከተማ 90 ፣ ለአርሲ ነጌሌ ከተማ 50 አስረክቧል።ከሌሎችም ከተሞች ጥያቄ እየቀረበላቸዉ ስለሚገኝ አዘጋጅቶ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ይገኛል።



ፎቶ 8 ሞዴል መንደር

2.7 የአረንጓዴ ልማት ስራ

በከተማው ውስጥ በተለያየ ቦታዎች የአረንጓዴ ልማት ስራ እየተሰራ ሲሆን በወንዞች ዳርቻ፣ በመንገዶች ዳርቻ በሚገኙ ክፍት ቦታዎች እና በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ የአረንጓዴ ልማት ስራዎች እየተካሄዱ ይገናሉ ይህ በመሆኑ ጤናማ እና ምቹ አካባቢን ለመፍጠር አስተዋአፆዎ የጎላ ነዉ።

2.7.1 የወንዝ ዳርቻ ልማት

2.7.1.1 8.1.1.ኤሳ የወንዝ ዳርቻ ልማት

ይህ የወንዝ ዳርቻ በፊት የቆሻሻ መጣያ የነበረ ሲሆን በአካባቢዉ ከፍተኛ ሽታ እንዲፈጠር ስለሚደርግ በህብረተሰቡ ላይ የተለያዩ የጤና ችግሮች ያስከትል ነበር። የወንዙ ዳርቻ ልማት ስራው የተጀመረው በ2009 ዓ.ም በULDP የበጀት ድጋፍ አማካኝነት ሲሆን 4 ሄክታር የሚሸፍን ነዉ። ይህ ልማት ዓላማ አድርጎ የተነሳዉ ቆሻሻ የበዛበትን ቦታ አረንጓዴ በማልበስ ከተማዉን ዕዱ እና አረንጓዴ ለማድረግ እና የስራ ዕድልም ለመፍጠር አላማ ያደረገ ነበር። በመሆኑም የልጆች መጫወቻ ፣ የስፖርት ማዘዉተሪያና ልዩ ልዩ መዝናኛዎችን አካቶ ይዟል። ይህን ቦታ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ መሀመድ አሚን፣ዲታና ጓደኞቹ የሚባል ማህበር እያስተዳደረዉ ይገኛል።ማህበሩ 5 ወንድ እና 1 ሴት በድምሩ 6 አባላት ያሉት ሲሆን ከአባላቱ በተጨማሪ 7 ሰራተኞች ቀጥሮ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።ማዘጋጃ ቤቱ በወር 25000 ብር በየወሩ ከዚህ ፕሮጀክት ገቢ ያገኛል።



ፎቶ 9 ኤሳ የወንዝ ዳርቻ ልማት (በፈር ዞን)

2.7.1.2 መልካ አዳ ወንዝ ዳርቻ ልማት

መልካ አዳ ወንዝ ዳርቻ በፊት የቆሻሻ ማስወገጃ (land fill) የነበረ ቦታ ሲሆን በአግባቡ መያዝ ባለመቻሉ ወንዙ ከመበከሉ ባለፈ ከፍተኛ ሽታ በመፍጠር በማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲያስከትል ቆይቷል። በ2014 ዓ.ም በULDP በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እና በማዘጋጃ ቤቱ አስተባባሪነት 8 ሔክታር የወንዙን ዳርቻ ማልማት ተችሏል። ይህ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የተለያየ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።ለምሳሌ

- ኮምፖስትን በመጠቀም አትክልት ማልማት በመቻሉ 74 የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን ማገዝ ፣
- የችግኝ ጣቢያ በዉስጡ ስለተቋቋመ የተለያዩ ችግኞችን ለማህበረሰቡ በማቅረብ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ይህ ቦታ ባሁኑ ጊዜ በግንባታ ላይ የሚገኝ ሲሆን ግንባታዉ ሲጠናቀቅ ለተጨማሪ 53 ሰዎች የስራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል።



ፎቶ 10 መልካ አዳ የወንዝ ዳርቻ ልማት(BUFFER ZONE)

ክፍል ሦስት

ማጠቃለያ

ሻሸመኔ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ስርአት ከመጀመሩ በፊት በከተማው የቆሻሻ አወጋገድ ስርአቱ ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ አልነበረም። በዚህም ምክንያት የከተማው ነዋሪ ለጤንነት ችግር የተጋለጠ ነበር። ከተማ አስተዳደሩ ስራ የጀመረው በችግሩ አሳሳቢነት ዙሪያ በአመራርና ባለሙያዎች ደረጃ በመወያየት ዕቅድ በማቀድ፣ ሕብረተሰቡን በማወያየት፣ ማህበራትን በማደራጀት፣ አመራሩንና ባለሙያዎችን በማጠናከር ስለ ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ስርአት ግንዛቤ በመፍጠር ነበር። ከተማ አስተዳደሩ በትኩረት መስራት በመቻሉ ከተማው በፊት ካለበት ዝቅተኛ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ተላቆ ዛሬ ሌሎችም ሊጎበኙ የሚችሉ ስፍራዎች ያሉት ከተማ እስከ መሆን ደርሷል።

በዕቅድ እየተመራ በቅንጅት በመሰራቱ የሚከተሉት ለውጦች/ውጤቶች ተገኝተዋል።

- በየቦታው ተዝረክርኮ ከተማውን ይበክል የነበረ ቆሻሻ በአሁኑ ጊዜ ሥርዓት እንድይዝ ተደርጓል
- የመንገድ ዳር ዲች/ቦይ በፊት በቆሻሻ ተደፍኖ ነዋሪውን ለጎርፍ አጋልጦ የነበረው በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ለውጥ ማሳየት ችሏል።
- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተሰርቶ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆኗል።
- በፊት በየቦታው ተዝረክርኮ የበሽታ መንስኤ የነበረው ቆሻሻ አሁን ሀብት ሆኖ የገቢ ምንጭ ሆኗል።
- ከደረቅ ቆሻሻ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- በየቦታው በቆሻሻነት ያስቸገረው የውሃ መያዣ ጠርሙሶች በአሻሽሎ መጠቀም አገልግሎት ላይ በመዋላቸው በስርዓት እየተሰበሰቡ በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ሆኗል።በመሆኑም በሕብረተሰቡ ዘንድ ቆሻሻ ገንዘብ መሆኑን እንዲያውቁት በተግባር ታይቷል።
- በርካታ ቁጥር ያላቸው በማህበር የተደራጁ ዜጎች የስራ ዕድል እንዲያገኙ አድርጓል።

በመሆኑም በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ ከተሞች ነባራዊ ሁኔታ በማየትና በማጥናት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ተፈጥሮ የሰጠንን ሀብት በአግባቡ በመያዝና በመንከባከብ ተጠቃሚ መሆን ይገባል።